ሀፓታይተስ ቢ አይን ቢጫ ከማድረግ ባሻገር ለከፉ የማይሰጥ በሽታ ነው?

ስለ ሃፓታይተስ ቢ ብዙ ማወቅ የሚገባን ነገሮች አሉ።

ICHS International Community HEALTH SERVICES

ይህ የአንድ የኢትዮጵያዊ ስደተኛ ቤተሰብ ታሪክ ነው።

ማሳሰቢያ፡ በዚህ ፍቶ ደገፍ የሃፕታይተስ ቢ ግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ የተሳተፉት ግለሰቦች ተዋንያን ናቸው። በመሆኑም ታሪኩ፡ የተዋንያንኑ ስሞችና እና ገጸ-ባህሪያት ልብወለድ ናቸው።

የትግስት ቤተሰቦች በኢትዮጵያ የማህበረሰብ ማእከል
የተሰጠውን የጤና ትምህርት ሲከታተሉ።



የሃፕታይተስ ቢ
አስተማሪ

ሀፕታይተስ ቢ በቫይረስ አማካይነት
የሚከሰት ጉበትን የሚያጠቃ በሽታ ነው።

የሃፕታይተስ ቢ እውነታዎች

- አብዛኛው ጊዜ ሰዎች በቫይረሱ ለመጠቃታቸው ምንም ዓይነት ምልክት ሳያሳዩ ይኖራሉ'። በአንዳድንድ ሰዎች ግን ትኩሳት፡ ከባድ ድካም፡ የሰገራ ግራጫ መሆን፡ የሽንት መደፍረስ እና የአይን ወደ ቢጫነት መቀየር የመሳሰሉ ምልክቶች ይታያሉ።
- ከሰሐራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት በሽታው እስከ አሁን ድረስ በስፋት ተንሰራፍቶ ይገኛል።
- በሽታው ይኑሮት ወይም አይኑሮት እርግጠኛ ለመሆን ብቸኛው መንገድ የደም ምርመራ ማድረግ ነው።

እቤት ከጤና ትምህርቱ መልስ።

እማዬ እና አባዬ የጤና ቀን በዓል ዝግጅቱ ወደዳችሁት? የጤና ባለሞያው ሀፕታይተስ ቢ የተባለውን በሽታ አስመልክቶ የሰጠው ገለጻ ታስታውሳላችሁ? ስለሱ ላነጋግራችሁ እፈልጋልሁ።

ስለ ጉበት በሽታ የተናገረው ማለትሽ ነው? እኛ አገር የወፍ በሽታ ነው የምንለው። አይን ቢጫ ያደርጋል።

አዎ በሽታው ሀፐታይተስ ቢ ይባላል። የጤና ባለሞያው እንዳለው በሽታው እኛ ከመጣንበት የዓለም ክፍል በብዛት ይታያል። ስለዚህ ምርመራ ብናደርግ ጥሩ ነው።

በመሆኑም ለሰኞ ጧት ከሐኪማችን ጋር ቀጠሮ ይዣለሁ። ከዛ በፊት ግን የደም ምርመራ ማድረግ ይኖርብናል።

የደም ምርመራ ሲያድርጉ

ይቅርታ ዶክተር ጆንሰን እንደምታውቂው ወላጆቼ እንግሊዘኛ
አጥርተው ሰለማይናገሩ አስተርጓሚ ብትጠሪላቸው ይሻላል።

መልካም እንግዲያውስ የስልክ አስተርጓሚ ላቅርብ።
የምትናገሩት ቋንቋ አማርኛ ነው አይደል?

አዎ

ጤና ይስጥልኝ።
እኔ አስተርጓሚያችሁ ነኝ ።

አስተርጓሚ ስልክ
ላይ ነው።

ወይዘሮ አልማዝ የደም ምርመራዎ ወጤት የሚያሳየው ከዚህ ቢፊት ለበሽታው ተጋልጠው እንደነበረና ግን ሰውነትዎ የተፈጥሮ በሽታ የመቋቋም ሀይሉ ተጠቅሞ ቫይረሱን እንዳስወገደው ነው። ዳግም በቫይረሱ ሊጠቁ አይችሉም።

ትግስት ከቫይረሱ ነጻ ብትሆኚም በሽታው ሊጋባብሽ ስለሚችል መከላከያ ክትባት መውሰድ ይኖሮብሻል።

አቶ ሐይሉ የርስዎ የደም ምርመራ የሚያሳየው በሽታው እንዳለብዎ ነው.። ሳይታውቅዎ ለዘማናት ቫይረሱን በሰወነትዎ ተሸክመውት ኖረው ስለሚሆንና ጉበትዎንም ነክቶት ስለሚሆን ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ጉበት ሓኪም አስተላልፍዎታለሁ።

እንደተረዳሁት ከሆነ ሀፐታይተስ ቢ የሚተላለፍው በወሲብ አማካይነት ነው።

አባቴ ደግሞ ሐይማኖተኛ ነው። ታድያ እንዴት ነው እንዲህ ዓይነቱ በሽታ ሊይዘው የቻለው?



በርግጥ ወሲብ በሽታው ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ሆኖም ግን ሀፐታይተስ ቢ በደም ንክኪ ማለትም በሽታው ካለበት ሰው በተበከሉ መርፌ እና ሊሎች የሰሉ ነግሮች እንዲሁም በወሊድ ጊዜ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ይችላል።

የመከላከያ ክትባት አጥረት ባለባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች በሽታው በነዚህ መንገዶች በሰፊው ይተላለፋል። ስለዚህ አባትሽ ተወልደው ያደጉት ኢትዮጵያ ወስጥ ስለሆነ ከነዚህ መንገዶች ባንዱ ምክንያት በሽታው ተጋብቶባቸው ሊሆን ይችላል።

ዶክተር ጆንሰን፡ ባለቤቴ ሀፐታይተስ ቢ ከያዘው ብዙ ጊዜ ከሆነው እንዴት እስከአሁን ድረስ ምንም ዓይነት ምልክት ሳያሳይ ኖረ?
ብዙ ሰዎች በሽታው እንዳለባቸው ሳያውቁት ለዘማናት መኖር ይችላሉ።


ግንኮ እኛ አገራችን የወፍ በሽታ የተለመደና ለከፉ የሚይሰጥ ነው።
ማለቴ ለጥቂት ቀናት ትታመሚያለሽ ከዛ በኋላ ትድኚያለሽ። አንዴ ታመሽ ከዳንሽ ደጎም ዳግም አትታመሚም?
ትክክል ነዎት ወይዘሮ አልማዝ። በአንዳንድ ሰዎች ላይ በሽታው ጊዜያዊ ነው። ምክንያቱም ሰውነታቸው የተፈጥሮ የመከላከያ ሐይል ስለሚያመነጭ ነው።
ሆኖም ግን በአንዳንድ ሰዎች ላይ ባለቢትዎንም ጨምሮ የተፈጥሮ የመከላከያ ሐይላቸው ቫይረሱን ሊያስወግደው ስለማይችል ምንም ምልክት ሳያሳዩ ለዘመናት (አስከ ሰላሳ ዓመታት) ቫይረሱን ተሸክመውት ይኖራሉ። በዚህ ጊዜ ወስጥ ግን ቫይረሱ ቀስ በቀስ ጉበታቸውን ያጠቃል። ለዚህም ነው የሀፐታይተስ ቢ በሽታ አድፍጦ ገዳይ የሚባለው።

ይህ በሽታ ማዳኛ መድሃኒት አለው?

እስከ አሁን ሀፐታይተስ ቢ መዳኛ መድሃኒት የለውም፡ ግን ጥሩው ነገር የጉበት ጉዳቱን የሚያዘገዩ መድሃኒቶች አሉ።

በሽታው ወደ ሌሎች ላለማጋባት ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብኝ?
ለአሁኑ በቆዳዎ ላይ የመቆረጥ ወይም የመድማት ሁኔታ ቢያጋጥም የደማው ቦታ ትንሽም ቢሆን በሚገባ መሸፈን፡ ስለት ያለባቸው ነገሮች እንደ ጺም መላጫ፤ የጥርስ መፋቂያ፤ የጆሮ ጊጣጌጥ ከመጋራት መቆጠብና በሽታው በወሲብ እንዳይተላልፍ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ነው።

ስለ ሀፕታይተስ ቢ ተጨማሪ መረጃዎች

- ከ 15-40% በሚደሩስ የበሽታው ተጠቂዎች በሽታው ወደ ከፋ የጉበት በሽታ ማለትም የጉበት መሻከር፡ የጉበት ካንሰርና ብሎም ሞትን ያስከትላል።
- የጉበት ካንሰር ምርመራ የመጀመሪያ ትንሹ እድሜ ለሌሎች ዘሮች 50 ዓመት ሲሆን ለአፍሪካውያን ወንዶች ግን 25 ነው ።

የሃፕታይተስ ቢ በሽታ እንዳይዛመት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

- በሽታው እንዳይዛመት ጥንቃቄ ከማድረግ በተጨማሪ ብቸኛው የመከላከያ መንገድ ሶስቱ ክትባቶ መውሰድ ነው።
- ሆኖም ግን ክትባቱ የሚሰራው በቫይረሱ ላልተጠቁ ሰዎች ብቻ ነው።

አባዬ ዶክተርዋ እንዳለችው ሳይታወቅህ ለዘመናት የሀፐታይተስ ቢ ተጠቂ ሆነህ ቆይተሀል። እናም እንደነገረችህ የበሽታው ጉዳት ማዘኒያ ወይም ማስታገሻ እንጂ ማዳኛ መድሃኒት የለውም። ይህ የተሰጠን የጽሁፍ መረጃ ምን እንደሚል ልንገርህ። ሀፐታይተስ ቢ ያለበት ሰው ራሱን መንከባከብ አለበት፡ ጤናማ ምግብ መመገብና አልኮሆል መቀነስ እንዲሁም ቫይታሚንና ሌሎች ጉበትን ሊጎዱ የሚችሉ መድሃኒቶች ከመውሰዱ በፊት ሐኪም ማማከር አለበት ይላል።

እንደምታውቂው መጠጥ የምቀምሰው አልፎ አልፎ ነው። ለዛውም የምጠጣው ጠጅ ነው።
ባህላዊ መጠጦችም ቢሆኑ አባዬ ጉበትን እኮ ሊጎዱ ይችላሉ። ስለዚህ መጠንቀቁ አይከፋም።

* የሀፓታይተስ ቢ በሽታ በመተቃቀፍ አይተላለፍም።

ተፈጸመ

ምስጋና
ጽሑፍ፡ መሐመድ አብዱልቃድር ና ማይክል መኪ
ትርጉም፡ መሐመድ አብዱልቃድር
አርታኢ ፡ ሄርበርት አቴንዛ
ዲዛይን፡ ቻርለስ ሊ
ፎቶግራፍ፡ ስቲቭ ሽልተን
ኢንተርናሽናል ኮምዩኒት ሄልዝ ሰርቪስስ

ADMINISTRATION

720 8th Ave S, 2nd Floor
Seattle, WA 98104

TEL 206.788.3650
TTY 206.788.3774

MAILING ADDRESS

PO Box 3007
Seattle, WA 98114-3007

INTERNATIONAL DISTRICT MEDICAL & DENTAL CLINIC

720 8th Ave S
Seattle, WA 98104

TEL 206.788.3700

HOLLY PARK MEDICAL & DENTAL CLINIC

3815 S Othello St
Seattle, WA 98118

TEL 206.788.3500

BELLEVUE MEDICAL & DENTAL CLINIC

1050 140th Ave NE
Bellevue, WA 98005

TEL 425.373.3000

SHORELINE MEDICAL & DENTAL CLINIC

16549 Aurora Ave N
Shoreline, WA 98133

TEL 206.533.2600

SEATTLE WORLD SCHOOL HEALTH CENTER

1700 E Union St,

Seattle, WA 98122

TEL 206.332.7160

ICHS PRIMARY CARE CLINIC AT ACRS

3639 Martin Luther King Jr. Way S
Seattle, WA 98144

TEL 206.788.3700

MOBILE DENTAL CLINIC

TEL 206.445.8454

www.ichs.com